# የአስር ቀን የአየር ሁኔታ ግምገማና እና ትንበያ መጽሔት

## ከጁላይ 1-10/2022 የነበረው የአየር

## ሁኔታ ግምገማ እና

## ከጁላይ 11-20/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

## ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ጁላይ 2022
አዲስ አበባ

**ርዕስ** **ገፅ**


እ.ኤ.አ ከጁላይ 1-10/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ ....3
ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 10 /2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ....4
ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 10 /2022 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት ....5
....5
ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 10 /2022 ድረስ የነበረው የዝና ብመጠን ....6
ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ....6
እ.ኤ.አ ከጁላይ 1-10/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ በእርሻ ሥራ....7
እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ....7
ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 10/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ....7
እ.ኤ.አ ከጁላይ 1-10/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ....8
እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ....8
ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 10/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ....8
እ.ኤ.አ ከጁላይ 11-20/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ ....9
እ.ኤ.አ ከጁላይ 11-20/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ....10
እ.ኤ.አ ከጁላይ 11-20/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ....11


## እ.ኤ.አ ከጁላይ 1-10/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ

ባለፉት አስር ቀናት ጠንከር ያለ እርጠበት አዘል አየር ወደ ሀገራችን ሲገባ የነበረ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የተስፋፋ የደመና ሽፋንና ዝናብ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ተስተዉሏል፡፡ በተጨማሪም አልፎ አልፎ ከተፈጠረዉ ጠንካራ የደመና ክምችት በአንዳንድ ስፍራዎች ላይ እስከ 113.0 በሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ በተለይም በጁላይ 02/ 2022 በባህርዳር ንፋስ ቀላቅሎ የጣለዉ 110 ሚ.ሜ ከባድ ዝናብ ቅፅበታዊ ጎርፍ በንብረት ላይ ጉዳት ማድረሱንና በጁላይ 06/2022 በፍቼ አካባቢ የጣለዉ መብረቅም በሰዉ ህይወት ላይ ጉዳት ማድረሱን የተሰበሰቡ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ በአጠቃላይ ባለፉት አስር ቀናት በትግራይ፣ በአማራ፣ በቤንሻንጉል-ጉሙዝ፣ በምዕራብና መካከለኛዉ ኦሮሚያ፣ በደቡብ ደጋማ ስፍራዎች፣ በሰሜን ሶማሌ፣ በሐረሪና ድሬዳዋ፣ በጋምቤላ፣ በደቡብ ብሄር ብሔረሰቦችና ህዝቦች፣ በሲዳማና ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ እንዲሁም በደቡብ አፋር አካባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከባድ ዝናብ ከተመዘገበባቸዉ ጣቢያዎች መካከል አንዳንዶቹን ለመጥቀስ ያህል በባህርዳር 110ና 36.6፣ በሻሁራ 48.7፣ በአለም ከተማ 75.0፣ በነጆ 113.0፣ በጨዋቃ 53.0፣ በነቀምቴ 47.2፣ በአሶሳ 51.6ና 50.4፣ በአቦቦ 50.0፣ በፉኝዶ 52.0፣ በማሻ 50.2፣ በአማን 60.4 በሚ.ሜ ይገኙበታል፡፡


ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም በትግራይና አማራ ክልሎች ዞኖች፣ በቤንሻንጉል፣ በጋምቤላ፣ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ሁሉም ዞኖች፣ በሁሉም የወለጋና ሸዋ ዞኖች፣ በቡኖ በደሌ፣ በኢሉ አባቦራ፣ በጅማ፣ በአርሲና ምዕራብ አርሲ፣ በምዕራብና ምስራቅ ሐረርጌ፣ በአፋር ክልል ዞን 03፣ 05፣ 02ና 04፣ በጉራጌ፣ በስልጤ፣ በሀዲያ፣ በሀላባ፣ በከምባታ ጠምባሮና ዳዉሮ ዞኖች ላይ ከ25-289 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ4-10 ቀናት ያህል ዝናብ የነበራቸዉ ሲሆን፤ በተቀሩት የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል፣ በሲዳማ ክልል ዞኖች፣ በአፋር ክልል ዞን 01፣ በባሌና ምስራቅ ባሌ፣ በጉጂና ምዕራብ ጉጂ፣ በሲቲና ፋፈን ዞኖች ላይም ከ5-25 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ 4 ላነሱ ቀናት ዝናብ ነበራቸዉ፡፡

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር በትግራይና አማራ ክልሎች ዞኖች፣ በቤንሻንጉል፣ በጋምቤላ፣ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵየ ክልል ሁሉም ዞኖች፣ በሁሉም የወለጋና ሸዋ ዞኖች፣ በቡኖ በደሌ፣ በኢሉ አባቦራ፣ በጅማ፣ በአርሲና ምዕራብ አርሲ፣ በምዕራብና ምስራቅ ሐረርጌ፣ በባሌ፣ በጥቂት የጉጂ፣ በአፋር ክልል ዞን 03፣ 05፣ 02ና 04፣ በጉራጌና በስልጤ ዞኖች ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ ነበራቸዉ፡፡


ካርታ 1   ኢ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 10 /2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 2    ኢ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 10 /2022 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት



**ካርታ 3    ኢ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 10 /2022 ድረስ የነበረው የዝና ብመጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር**





| | | | |
|---|---|---|---|
| የወቅቱን ዝናብ የማያገኙ አካባቢዎች | ከመደበኛ በታች | መደበኛ | ከመደበኛ በላይ |

# እ.ኤ.አ ከጁላይ 1-10/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ በእርሻ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

በጁላይ የመጀመሪያው አስር ቀናት ለክረምት ዝናብ መኖር አመቺ ሁኔታ የሚፈጥሩ የአየር ሁኔታ ክስተቶች የተሻለ ጥንካሬ የነበራቸው በመሆኑ፤ በአብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ከቦታ ቦታ በመጠን ይለያይ እንጂ በስርጭት ብዙ አካባቢዎችን ያዳረሰ የእርጥበት ሁኔታ እንደነበራቸው ከተለያዩ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች የተሰበሰቡ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ይህም ሁኔታ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ ለሆኑት የሀገሪቱ ክፍሎች አዎንታዊ ሚና የነበራቸው ሲሆን በተለይም አስቀድመው ለተዘሩና በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የተለያዩ ሰብሎች ሆነ ለቋሚ ተክሎች የውሀ ፍላጎት መሟላት ጥሩ ሁኔታ እንደነበረው መገንዘብ ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ በተለይም በመካከለኛው ኢትዮጵያ አንዳንድ ሥፍራዎች የነበረው ከባድ ዝናብ የአፈር ውስጥ እርጥበት መብዛት እና በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ለወንዝ መሙላትና ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች ላይ ለጎርፍ መከሰት እንዲሁም ተከታታይነት የነበረው እርጥበታማ ሁኔታ በሰብል ማሳዎች ላይ የውሃ መተኛት ያስከተለ ሲሆን፤ ይህም ሁኔታ እየተከናወነ በሚገኘዉ የእርሻ ስራ እንቅስቃሴ ላይ አሉታዊ ጎን ነበረው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በመካከለኛውና በምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች የተገኘው እርጥበት በተለይም ባሳለፍናቸው ቀናት ካገኙት እርጥበት ጋር ተዳምሮ የመጠጥ ውሀ አቅርቦትንም ሆነ የግጦሽ ሳር ልምላሜና የተፈጥሮም ሆነ የሰው ሰራሽ ምንጮችን ከማጎልበት አንጻር የጎላ አስተዋጽኦ ነበረው (ካርታ 4) ፡፡


ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 10/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



# እ.ኤ.አ ከጁላይ 1-10/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

እ.ኤ.አ 1-10 ጁላይ 2022 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ የነበረው ገፅታ በተመለከተ የተሻለ የእርጥበት መጠን በአብዛኛው አባይ፣ ባሮአኮቦ፣ ተከዜ፣የላይኛው እና መካከለኛው አዋሽ፣ ኦሞጊቤ፣ ስምጥሸለቆ፣ አፋር ደናክል የላይኛው ገናሌዳዋ እና ዋቤሸበሌ ተፋሰሶች ላይ ከእርጥበታማ እስከ ከፍተኛ እርጥበት አግኝተዋል፡፡ በተጨማሪም መጠነኛ እርጥበት የተሰተዋለባቸው ተፋሰሶች የመካከለኛው ገናሌዳዋ እና ዋቤሸበሌ እንዲሁም በጥቂት የታችኛዉ አዋሽ ተፋሰሶች ናቸው፡ የተቀሩት በአብዛኛው የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ በከፊል ደረቅና ደረቅ ሁኔታ አመዝኖ ተሰተውሏል (ካርታ 5) ፡፡

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 10/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



# እ.ኤ.አ ከጁላይ 11-20/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ በጁላይ ሁለተኛው አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በይበልጥ እየተጠናከሩ በመሄድ ከቀዳሚው አሥር ቀናት የተሻለ የክረምት ዝናብ በወቅቱ የዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ የሚዘወተርበት ጊዜ ነዉ።

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ተጠናክረው ሊቀጥሉ እንደሚችሉና ከዚሁም ጋር ተያይዞ በመጠንም ሆነ በሥርጭት የተስፋፋ ዝናብ ሊኖር እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ። በተጨማሪም አልፎ አልፎ ከሚፈጠረዉ ጠንካራ የደመና ክምችት በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ ቅፅበታዊ ጎርፍ የማስከተል አቅም ያለዉ ከባድ ዝናብ ሊኖር ይችላል፡፡

በአጠቃላይ በሚቀጥሉት አሥር ቀናት <u>ከኦሮሚያ ክልል በጂማ፣ በቡኖ በደሌ፣ በኢሉአባቦራ፣ በምሥራቅ እና ምእራብ ወለጋ፣ በቄለምና ሆሮ ጉዱሩ ወለጋ፣ በሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች አዲስ አበባን ጨምሮ፣ በሁሉም የአማራ ክልል ዞኖች፣ የትግራይና የቤንሻንጉል-ጉሙዝ ክልሎች ዞኖች፣ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ በሸካና ከፋ፣ ከደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል የጉራጌ፣ የስልጤ፣ የሀዲያ፣ የወላይታ፣ ከምባታ፣ የሀለባ ዞኖች፣ የሲዳማ ክልል ዞኖች፣ ከአፋር ክልል የዞን 03ና 05፣ በአብዛኛው መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ የሚጠበቅ ሲሆን፤ ከሚጠናከሩ የደመና ክምችቶች በአንዳንድ ሥፍራዎች ላይ ነገደጓድ አዘልና በረዶ የቀላቀለ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ሊከሰት ይችላል። በተጨማሪም ምዕራብ እና ምሥራቅ ሐረርጌ እንዲሁም የአርሲና ምዕራብ አርሲ፣ በባሌ፣ የሐረሪና ድሬዳዋ፣ ከሱማሌ ክልል የሲቲና ፋፈና ዞኖች፣ የጋምቤላ ክልል ዞኖች፣ የአፋር ክልል ዞን 01፣ 02ና 04፣ የቤንች ሸኮ፣ የምዕራብ ኦሞ፣ የጋሞና ጎፋ፣ የጌዴኦ ዞኖች ከመደበኛ ጋር የተቀራረበ ዝናብ እንደሚኖራቸዉ ይጠበቃል፡፡</u>

## እ.ኤ.አ ከጁላይ 11-20/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመደበኛ ሁኔታ በጁላይ ሁለተኛው አስር ቀናት በአብዛኛዎቹ የክረምት ሰብል አብቃይ በሆኑት አካባቢዎች እረጥበቱ ይበልጥ እየተጠናከረ  የሚሄድበት ጊዜ ሲሆን ከግብርና እንቅስቃሴ አንጻር አሰቀድመው ለተዘሩ ሰብሎች የሚያስፈለጋቸውን የአፈረ ውስጥ እርጥበት በበቂ ሁኔታ የሚያገኙበት እና በተጨማሪ ለሚዘሩ ሰሎች ምቹ ሁኔታ የሚፈጠርበት ጊዜ ነው።

በተሰጠው የአስር ቀን ትንበያ መሠረት ለዝናብ መፈጠር አስተዋጽኦ የሚያደርጉ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች እየተጠናከሩ ሊሄዱ እንደሚችልና በመጠንም ሆነ በስርጭት ብዙ አካባቢዎችን የሚሸፍን እርጥበት እንደሚኖር እንዲሁም በአንዳንድ አካባቢዎች ቅጽበታዊ ጎርፍ ሊያስከተል የሚችል ከባድ ዝናብ ሊኖር እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ይህም ሁኔታ የክረምት ወቅት ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ ለሚጠበቀው የግብርና እንቅስቃሴ ጥሩ ጎን የሚኖረው ሲሆን በአጠቃላይ ከላይ በትንበያው ላይ በተጠቀሱት አካባቢዎች በአብዛኛው ከመደበኛና ከመደበኛ በላይ የሆነ ዝናብ የሚያገኙ ሲሆን፣ ይህም ሁኔታ የአፈር ውስጥ እርጥበትን ከማሻሻል አንፃር አስቀድመው የተዘሩና በተለያየ የዕድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የበልግም ሆነ የረጅም ጊዜ የመኸር ሰብሎች እንዲሁም ለተለያዩ የቋሚ ተክሎችና የጓሮ አትክልቶች የውሀ ፍላጎታቸውን ከማሟላት አንፃር ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ በአንፃሩ በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ የሚጠበቀው ከባድ ዝናብ በተለይም ባሳለፍናቸው ቀናት በተከታታይ ዝናብ በማግኘት ላይ በሚገኙና ውኃ የመሸከም አቅማቸው ከፍተኛ የሆነ የአፈር አይነት ባለባቸው ቦታዎች ላይ የአፈር ውስጥ እርጥበት መብዛት፣ እንዲሁም ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች ከአፈር መሸርሸርም ሆነ ከመሬት መንሸራተት ጋር የተያያዙ ችግሮችን ሊያስከትል ስለሚችል አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነዉ፡፡ በተጨማሪም ከእርጥበት መብዛት ጋር ተያይዞ የአረም መጨመር ሊከሰት ስለሚችል አሰፈላጊው ቅድመ ጥንቃቄ እነዲደረግ ይመከራል። በሌላ በኩል በአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የሚጠበቀው እርጥበት በተለይም ባሳለፍናቸው ቀናት አካባቢዎቹ ካገኙት የተሻለ እርጥበት ጋር ተዳምሮ የመጠጥ ውሀ አቅርቦትና የግጦሽ ሳር ልምላሜ  ከማሻሻል  አንጻር ጥሩ ጎን ይኖረዋል፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ጥሩ አስተዋጽኦ እንደሚኖረዉ ይጠበቃል፡፡

## እ.ኤ.አ ከጁላይ 11-20/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

የክረምቱ ዝናብ በሚቀጥሉት አስር ቀናት ውስጥ በተጠናከረ ሁኔታ የክረምት ዝናብ በሚያገኙት ተፋሰሶች ላይ ቀጣይነት እንዳለው ትንበያው ያመላክታል፡፡ ይህንን ተከትሎ በአብዛኛዉ በአባይ፣ በተከዜ፣ በባሮአኮቦ፣ በአዋሽ፣ በላይኛውና በመካከለኛው ስምጥሸለቆ፣ በኦሞጊቤ፣ በአፋር ደናክል፣ በላይኛው ዋቤ ሸበሌ እንዲሁም በገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች ላይ ከከፍተኛ እርጥበት እስከ እርጥበታማ መጠን እንደሚያገኙ የሚጠበቅ ሲሆን፤ ከላይ በተጠቀሱ ተፋሰሶች ላይ በሚኖረው ተከታታይ እርጥበት የውሃ ስርገቱን ስለሚቀንሰው የሚገኘው ዝናብ በአብዛኘው ጎርፍ የመፍጠር አቅሙ ከፍተኛ ሊሆን እንደሚችል ትንበያው ይጠቁማል፡፡ ይህንን ተከትሎ ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ ቦታዎች ቅፅበታዊ ጎርፍ እና የመሬት መንሸራተት ሊከሰት ሰለሚችል ክትትልና ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በሌላ በኩል የታችኛው ስምጥ ሸለቆ፣ አፋር ደናክል፣ በጥቂት የላይኛዉ ኦጋዴን ተፋሰሶች ላይ ከእርጥበታማ እስከ መጠነኛ እርጥበት ሊኖራቸው እንደሚችል ይጠበቃል፡፡ የተቀሩት ተፋሰሶች ደረቅና ከፊል ደረቅ ሁኔታ ላይ እንደሚቆዩ ይጠበቃል፡፡